★ዴሞክራሲያ★
* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን *

ዴሞ ቅጽ 43 ቁ. 2 ኅዳር/ታኅሣስ 2010

# ወጣቱ ትውልድና የዛሬው ግዳጁ

በኢትዮጵያ ታሪክ የዕልፍ ዓመታት ክንዋኔች ውስጥ በጉልህ ጎልተው ከሚታዩ አኩሪ የትውልድ ቅርሶች መሀል ፤ እስከዛሬ በሰፊው የሚወሱትና እንደኮከብ ተፈንጥቀው የሚታዩት ፤ የሀገርን ነጻነት ከተለያዩ ቅኝ ገዚዎችና ወራሪዎች ተከላክሎና ጠብቆ ማቆየትና ለተተኪው ትውልድ የማስረከብ ክስተቶች ናቸው። ይህ ታላቅ ሀገራዊና ሕዝባዊ ግዳጅ ግቡን ሊመታና ሊሳካ የቻለው በየጊዜው የነበሩ ኢትዮጵያውያንና መሪዎቻቸው ዘርና ሃይማኖት ሳይለያያቸው፣ በአንድነት ቆመው በመታገላቸው እንደነበር ታሪክ የዘከረው ሐቅ ነው።

የቅርቡን ታሪካችንን እንኳን ብንመለከት፤ የጣሊያን ፋሽስት ጦር አገራችንን ቅኝ ግዛት በማድረግ ሊገዛን በመጣበት ወቅት ህዝቡ ከዳር እስከዳር ተነስቶ በአንድነትና በፈቃደኛነት ከፍተኛ መስዋዕት ከፍሎ ሀገሩን ታድጓል። ያኔም እንዳሁኑ ልዩ ልዩ ሃይማኖትም ሆነ ብሔር/ብሔረሰብ የነበረ ቢሆንም፤ በጎሳ ክፍፍል ሀገሩን ለድርድር አላቀረበም። እንዲያውም ጠቅላላው ሕዝብ ሃይማኖት የግል፣ ዘር የቤተሰብ፣ ቋንቋም የዘውግ ወይም የጎሳ ፤ ሀገር ግን የጋራ የሁላችንም እናት ናት ብሎ፤ ከደቡብ፣ ከሰሜን፣ ከምስራቅና ምዕራብ ተነስቶ፣ ዘመተ እንጂ ፤ “የአክሱም ሀውልት ለወላይታው ምኑ ነው” ብሎ፤ እንደዛሬዎቹ ባንዶችና የባንዶች ውላጆች፤ አልተሳለቀም፣ ሀገርንም አልካደም።

የታህሣሥ ወር በመጣ ቁጥር ባለፉት ሥርዓቶች ወጣቱ ትውልድ ለሕዝቡ መብት ፣ ለነፃነት፣ ለዕኩልነትና ለሀገር ልዕልና ባካሄደው ረጅም ተጋድሎ ለውጥ እንዲመጣ ያደረገው አስተዋፅዖ ዛሬም ሲታወስ ይኖራል። ይሁንና፤ ይህ ታጋይ ትውልድ በከፈለው መስዋዕትነት መጠን ያለመውም ሆነ ተገቢ የሆነው ለውጥና መሻሻል አልተገኘም። በየወቅቱ ሀገሪቱ ለሕዝብ ምንም ደንታ በሌላቸው አገዛዞች መዳፍ ሥር ወደቀች። ለሕዝብ ስቃይና መከራ ፣ ረሀብና ጉስቁልና ምንም የማይሰማቸው ፣ ራስ ወዳድና ጨቋኝ ቡድኖች፣ እንዲሁም ሕግና ደንብ የማይገዛቸው አረመኔ መሪዎች ተፈራረቁባት።

ባለፉት 60-70 ዓመታት እንኳን የሆነውን ስንቃኝ፤ ከአምስቱ ዓመታት የጣሊያን ወረራ በኋላ ፤ ተጋድሎ አድርገው ንጉሡን ወደ ሀገር እንዲመለሱ ያደረጉ ጀግኖች አርበኞች ከጥቂቶቹ በቀር ብዙዎቹ የሚገባቸውን ክብር ሳያገኙ ገሸሽ የተደረጉበትን ሁኔታ ተመልክተናል። ስመጥር ከነበሩት መሀልም እንደ እነበላይ ዘለቀና ታከለ ወልደሐዋሪያት የመሰሉትን ሀገር ወዳድ አርበኞች ለግዞት ዳርጎ፤ ሀገሪቱን ለጣሊያን ሸጠው ሕዝባቸውን በግልጽ የከዱትን ባንዶች የሾመው፣ የአፄ ኃይለ ሥላሤ ንጉሣዊ አገዛዝ እንደነበር የሚታወቅ ነው። ይህንን ክስተት ለማሳየት ነበር “ወይ ሀገሬ፣ ሞኝ ነሽ ተላላ፤ የሞተልሽ ቀርቶ የገደለሽ በላ” ተብሎ የተገጠመው።

ይህንን የግፍ አገዛዝ አልቀበልም በማለት፤ መሬት ላራሹ ይሰጥ ፣ ሰብዓዊ መብቶች ይከበሩ፣ ዘውዳዊ አገዛዝ ይወገድ፣ በሚል መፈክር ሕዝብ ከአጽናፍ አጽናፍ ተነስቶ ሥርዓቱን ሲያናጋ ፤ በወቅቱ ታጥቆና ተደራጅቶ የቆየው የሥርዓቱ ወታደርና የፖሊስ ኃይል እንዲሁም ሌሎች የሥርዓቱ ጠባቂና ተከላካይ የነበሩ ኃይላት ሥልጣንን ጨበጡ። በበታች ሹማምንትና መኮንኖች እየተመሩ፣ ከሕዝብ ጎን የቆሙ መስለው ፤ የፖለቲካ ሥልጣንን ጠቀለሉ። የአብዮቱ መሪዎች እኛ ነን ብለውም አወጁ። ግዳጃችንን ፈጽመን ወደየካምፓችን እንመለሳለን በማለት ሲምሉና ሲገዘቱ የነበሩት የወታደራዊ ደርግ አባሎች ለ17 ዓመታት፣ ሥልጣናቸውን መከታ አድርገው ህዝብንና በዓብዮቱ ግንባር ቀደም ሚና የነበራቸውን በርካታ ተራማጅ ኃይላትንና ወጣቶችን በቀይ ሽብር ዘመቻቸው ጨፈጨፉ፣ በእስርና በምርመራ አሰቃዩ፤ አገር ጥለው እንዲሰደዱ አደረጉ። ሕዝብንና ሀገርን እርቃኑን አስጥተው ፣ ለሀገር ሲል ህይወቱን ለመስጠት ዝግጁ የነበረውን ብርቅዬ ትውልድ አካሉን መትረው፤ አጥንቱን አድቅቀው፤ አገሪቱን ትውልድ አልባ አደረጓት። በመጨረሻም ፀረ-ሕዝብ፣ ፀረ-ሀገረና አረመኔ ለሆነው ወያኔ ዘረኛ ቡድን አገሪቱን አስረክበው፣ ፈረጠጡ።

በሥልጣን የተተካውም የወያኔ ቡድን ገና ከጥንስሡ ለኢትዮጵያና ሕዝቧ ከፍተኛ ጥላቻ ያለው ፤ የከሀዲዎችና የባንዶች ጥርቅም ሲሆን፤ ሕዝቧን በቋንቋና በጎሳ ከፋፍሎ ፤ የሀገሪቱን ሀብት ዘርፎና እራሱን አበልጽጎ፣ ለታሪካዊ ጠላቶቿ አጋልጧት ለመሄድ የመጣ ቡድን ለመሆኑ አሁን ለብዙዎች ግልጽ እየሆነ የመጣ ጉዳይ ሆኗል። ወያኔ ገና አዲስ አበባን ተቆጣጥሮ ሥልጣን ከመቀዳጀቱ በፊት ከትግራይ ጀምሮ በርካታ አገር ወዳዶችንና ቤተሰቦቻቸውን የፈጀ መሆኑ ይታወቃል። ባለፉት 26 ዓመታት የሥልጣን ዘመን ይህ ስመ ጥፉ ቡድን በሕዝብና በሀገር ላይ ያደረሰው በደል ተዘርዝሮ የሚያልቅ አይደለምና በደፈናው ቤቱ ይቁጠረው ብሎ ማለፉ የሚሻል ሳይሆን አይቀርም።

የወያኔ መሪዎች በወልቃይት ጠገዴ ፣ በአርማጭሆና በጎንደር እልፍ ዓዕላፍ ኢትዮጵያዊያንን ገድለዋል፣ አጥፍተዋል፤ አሰድደዋል፤ አሰቃይተውና አስረው ከጥቅም ውጪ አድርገዋል። በኦሮሚያ፣ በደቡብ ክልል፣ በጋምቤላ፣ በአጋዴን...ወዘተ ያደረሱት ጭፍጨፋና ግድያ መዘረዝር አዳጋች ሲሆን አሁንም በሰፊው የቀጠለ መሆኑ እየተሰማ ነው። አጋር የሚሆኗቸውም በሕዝብ ላይ የሚደርሰው ይህ ሁሉ በደል ምንም የማይሰማቸው ከሁሉም ዘርና አካባቢ የተውጣጡ ባንዳዎች አገልጋይዎችና ማፍያዎች አላጡም። የሕዝብ ወገን መስለው፣ ሥርዓቱን የሚያገለግሉ፤ ተቃዋሚ መስለው፣ ሕዝብን እያታለሉ ወጣቱንና ታጋዩን ክፍል ሰርገው ገብተው ፣ በየሥራ ቦታዎችም ሆነ በዩኒቨርሲቲዎች ሕዝቡንና ተማሪውን መስለው፤ እየጠቆሙ ታጋዮችን የሚያስገድሉና የሚያሳስሩ በርካቶች አገግልጋዮች ተፈጥረዋል። ወደፊትም ይኖራሉ።

ይሁን እንጅ በአሁኑ ጊዜ ትግሉ ተፋፍሞ ሕዝቡ የወያኔን ሴራ በጣጥሶ፣ ከታጠረለት የክልልና የቋንቋ አጥር ውጭ ወጥቶ በሃይማኖትና በጎሳ ልዩነት የተጣለለትን ወጥመድ በዘዴ ተሻግሮ፤ አማራና ኦሮሞ፣ እስላምና ክርስቲያን ነህ ተብሎ የተረጨበትን የጥላቻ መርዝ ማርከሻው የሆነውን የአንድነት መሳሪያ በጁ ይዟል። አንድነቱን እያጠናከረ በአምባገነኖች ላይ ትግሉን በማራመዱ በከፍተኛ ደረጃ የደነገጠውና ብርክ የያዘው በሥልጣን ላይ ያለው ወያኔ ብቻ ሳይሆን፣ ጥቃቅንና ታሪካዊ ችግሮችን አጉልተው ሕዝብን ለመከፋፈል ጥረት ሲያደርጉ የነበሩ ጠባቦችና ፀረ-ኢትዮጵያ ኃይሎችንም ጭምር ነው።

ከሁሉም በበላይ፤ በዚህ በአፍሪካ ቀንድ አካባቢና ዙርያ የበላይነታቸው ተጠብቆ እንዲቆይ የሚፈልጉ ኃይላትም በሀገራችን ኢትዮጵያና ሕዝቧ ላይ የተንሰራፋውን ቡድን ሲረዱና ሲደግፉ የቆዩ የውጭ ኃይሎችም ከመከራችን እንድንዘፈቅ የበኩላቸውን አስተዋፅዖ እያደረጉ ናቸው። ዛሬም የሕዝቡን ቆርጦ መነሳት ተረድተው ፣ ሲሆን ይህንኑ እርጉም አገዛዝ ቀለም ቀባብተው ግለሰቦችን ቀያይረው ፣ አቀራረብና ቅርጹን ላይ ላዩን ለዋውጠው ፤ ተለጣፊና እርባና የሌላቸወን ተቃዋሚ

ተብዬዎች እንዲያጅቧቸው አድርገው ፤ ለውጥ እንደመጣ አስመስለው መሰሪ አገልጋዮቻቸውን (ሪፎርም የሚል ካባ አልብሰው) በሕዝብ ጫንቃ ላይ ዳግም ሊጭኑ መሯሯጥ ጀምረዋል። ይህ ባይሆን ደግሞ ከውጭም ሆነ ከውስጥ ይጠቅሙናል የሚሏቸውን ፣ ለነሱ የተገዙ አስመሳይ ተቃዋሚዎችን አዘጋጅተው ከሕዝብ ይሁንታ ውጭ መንበረ ሥልጣን ላይ ለማስቀመጥ በመሯሯጥ ላይ መሆናቸው ያደባባይ ሚስጥር ከሆነ ሰነባብቷል። ከውጭዎቹ አምባ ሌላም ሴራና ተንኮል ሊዶለት እንደሚችል ፣ ገምቶ መከላከያውን ማሰብ የብልህ ታጋዮቻችንና ወጣት መሪዎች ንቁ የቤት ሥራ መሆን ይገባዋል እንላለን።

ከላይ እንደተመለከተው፣ ያለፈውን ታሪካችንን በጥሞና የምንመረምረው፣ የዛሬውን ውጥንቅጥ ሁኔታ ተረድተን የወደፊቱን የሚያዋጣ አቅጣጫ ለመትለም ስለሚረዳንም ነው። ለእውነተኛ ሕዝባዊና ሀገር አድን ለውጥ ስንነሳ ፤ እስካሁን የተከፈለውን እጅግ የላቀና የበዛ መስዋዕትነት፣ የጠፋውን ህይወትና የፈሰሰውን ደም ስናስብ ፤ ያገኘነው ውጤት እጅግ አንስተኛና ኢምንት ነውና “ለምን ?” ብለን መጠየቅና ካለፈው ተምረን የሕዝብ ጠላቶችን አስወግደን ፣ አስተማማኝ ለውጥና ሰላም፤ የሕዝብ የበላይነት፤ የሥልጣን ምንጭነት የሰፈነባትን ሀገር ተባብረን ለመገንባት የምንችልበትን ሁኔታ መፍጠር ታላቁ ግባችን መሆኑን በጽሞና መገንዘብ አለብን። ስለሆነም፣ አሁን በቅርቡ በተያዘው መንገድ፣ ከታሰርንበት የቋንቋና የጎሳ አጥር ተሰፈንጥረን ወጥተን ፣ ትግላችንን እንደ ሰንሰለት ከሁሉም ፀረ-ወያኔና ዴሞክራሲዊ የኢትዮጵያ ልጆች ትግል ጋር በሰከነ መንፈስና በተደራጀ መልኩ መያያዝ ይኖርብናል። እየተናበብንም ይህንን ሥርዓት ከሥረ-መሰረቱ ነቅለን፣ ለችግሮቻችን ሁሉ ዘላቂ መፍትሄ የምናገኝበትን ሁኔታ መፍጠር ይገባናል።

ኢሕአፓ ላለፉት አሥርተ ዓመታት ሲታገልለት የቆየው እስካሁንም በጽናት የቀጠለው በዚሁ አቅጣጫ ሕዝብን እየቀሰቀሰና እያዘጋጀ ነበር። ዛሬም እንደዚሁ። ቀድሞ ያልተዘጋጀ ፣ ያልተደራጀ ትግል፣ ምንም ጥሩ ዓላማና ትክክለኛ አመለካከትና ራዕይ ቢኖረውም ፣ ለድል አይበቃም። የተደራጁ ጮሌዎች፣ በባዕዳን ተጠፍጥፈው የተበጁ ቡድኖች በድንገት ተከስተው ዋና ተዋንያን ይሆኑና ሕዝብ በከፍተኛ መስዋዕትነት የተቀዳጀውን ድሉን ይቀሙታል። በራሳችን የቅርብ ታሪክና በሌሎችም እንዲሁ የታየ ነው። በየካቲት 66 ዓ/ም ሕዝብ  በነቂስ ተነስቶ፣ ሃይማኖት፣ ቋንቋና ዘር ሳይለየው፣ እድሜና ፆታ ሳያግደው እጅ ለጅ ተያይዞ ታግሎ፤ በወቅቱ ተንሰራፍቶ የነበረውን ዘውዳዊ ሥርዓት ከሥር መሰረቱ ነቅሎ፤ ዴሞክራሲዊት ሀገርን ሊጎናጸፍ በሂደት ላይ እያለ ፣ ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ከሁሉም የትግሉ ተሳታፊ የሕዝብ ክፍል ተቋቁሞ ሥልጣንን እንዲረከብ ሀሳብ እየቀረበ ባለበት ወቅት፤ ተደራጅቶና ታጥቆ የቆየው የወታደሩ ክፍል ከሥልጣን ላይ ጉብ ማለቱን ታሪክ ይነግረናል። በግብፅም የፀደይ አብዮት የታየው ይሄው ነበር። ከዚህም በላይ ብዙ ምሳሌዎችን መጥቀስ ይቻላል። ያለፈው ታሪክ የሚያስተምረን ቁም ነገር ግን ሕዝብ አዕላፍ ልጆቹን ገብሮ ፣ ያገኘውን ውጤት ለማንም  ለድርድር ማቀረብ የሌለበት መሆኑን ነው።

ማንኛውም ድርድር መነሻውና መድረሻው ፤ የመከራው ሁሉ ምንጭና ለሰላምና እድገቱ እንቅፋት የሆነውን አሸባሪ አገዛዝ ከስር መሰረቱ ነቅሎ ማስወገድ ላይ የተመሰረተ መሆን ይገባዋል። ለዚህ ሁሉ ጣጣና መከራ ከዳረጉንና ኢትዮጵያንና ጎስቋላውን ሕዝቧን አሳልፎ ለሻዕቢያና ወያኔ ያስረከበንን የለንደኑን ድርድርና የአደራዳሪዎቹን ሴራና ደባ ማስታወሱ ተገቢ ነው። የሚገርመው ግን እነዚያው በደል የፈጸሙብን  ሰዎች ተመልሰው በሽምግልና ስም ሊያታልሉን  ሲሟሟቱ እየታዘብን ነው - የሰሞኑን የነሔርማን ኮሆንን ቧልት ያጤኗል። የወጋ ቢረሳ የተወጋ ግን እንዴት ሁኖ እንላቸዋለን።

ዛሬ ላይ ሆነን ከትላንት እየተማርን የወደፊቱን እየቃኘን ሁሉንም መሰናክሎች እያለፍን በቆራጥነትና በብልሀት እንገሰግሳለን። ሊከፋፍሉንና ሊያጨራርሱን ሲጥሩ ፣ እምቢኝ እኛም ነቅተናል ጉድጓድ ምሰናል ብለን አንድነታችንን

አጥብቀን ፣ በመሀላችን የሰገሰጓቸውን ሰላዮችና ቆስቋሾች ነቅሰን እያወጣን፤ ለእውነተኛ ለውጥና በአንድነታችን ላይ ለተመሰረተ ዴሞክራሲዊ ሥርዓት ምስረታ የሁሉንም ሴራ አከሽፈን ወደፊት እንሄዳለን። ከዚህ ከደረስንበት አማራጭ የለሽ የጋራ ጉዞና ትሥሥር ወደ ኋላ ሊመልሱን የሚሞክሩ በጥላቻ የታወሩ ሁሉም ዓይነት ጠባቦችና የኋላ ተመልካቾች ውዥንብር ከእንግዲህ ቦታ የሚሰጠው እንዳልሆነ መከራችን አስተምሮናል።

ከዚህ ወጥመድና አረንቋ ተሻግረን ከፍተኛ የትግል ደረጃ ላይ ደርሰናል። እየተደራጀንና እራሳችንን እየተከላከለን አንድ በአንድ አካባቢያችንን ከአረመኔው የወያኔ መዋቅርና መንጋጋ እያላቀቅን እየበጣጠስን ትግላችን ካካሄድን ሥርዓቱ በሰደድ እሳት ተቃጥሎ የሕዝብ የበላይነት ይለመልማል። ሁሉንም የሕዘብ ክፍል፣ ወገን ወጣቱን አዛውንቱን፣ ሴቶችን እናቶችን፣ ሰራተኛና ገበሬውን ፣ ወታደሩን ሁሉ በህቡዕም ሆነ በሚመቸው ዘዴና መንገድ ሁሉ አደራጅቶና አካቶ ማሳተፍ ይበልጥ አስተማማኝ ውጤት ይኖረዋል። ዛሬ ከዳር ሆኖ የሚመለከት ዜጋ ሁሉ፣ አቋም ይዞ ትግሉን ይቀላቀል፤ እራሱን፣ ሕዝብን/ሀገሩን ያድን፤ በተለይ ወያኔ አይወክለንም የሚለው የትግራይ ከልል ኢትዮጵያዊ ምሁር፣ ወጣት ሁሉም አቋሙን ግልጽ ያድርግ። በሚቻለው መንገድ ሁሉ ትግሉን ይቀላቀል፤ ድምጹን ያሰማ ወያኔን ከራሱ ላይ ያውርድ።

የትግራይ ሕዝብ በታሪካችን፣ ለሀገሩ ለዳር ድንበሩ፣ ለኢትዮጵያዊነቱ ከጠላት ጋር እየተጋፈጠ ይህ ነው የማይባል መስዋዕትነትን ያስመዘገበ ዜጋችን ነው። ዛሬም፣ ወያኔ ተብየው በሀገር ላይ የመጣ፤ በሕዝብና በሀገር አንድነት ላይ የዘመተ የማፊያ ቡድን መሆኑን ተገንዝቦ ከተቀረው ኢትዮጵያዊ ወገኑ ጋር በመቆም ሊታገለው ይገባል። ወያኔ በትግራይም የሕዝብ ይሁንታ እንደሌለው ሕዝቡ ባጠቃላይ በተለይም ወጣቱ እራሱ ከማንም በላይ ጠንቅቆ ያውቀዋል። በትግራይ የሚካሄደው ኢኮሚያዊ ሆነ ማኅበራዊ እንቅስቃሴ አስተዳደር ሆነ ምርጫ እንደየትኛውም የኢትዮጵያ ክፍል ወያኔ የሚቆጣጠረው ከመሆኑን በላይ ለቡድኑ ኪስ ማደለቢያና ለሥልጣን ማቆያ እንጂ በምንም ዓይነት ለሕዝብ ጥቅም እንዳልሆነ የተመዘገበ ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ (የትግራይ ሕዝብን ጨምሮ)፤ እሱ/ሕዝቡ የሥልጣን ምንጭ የሆነባት፤ አንድነት በዕኩልነት የሰፈነባት፤ ፍትህ ብልጽግና በተግባር የሚውልባት ኢትዮጵያን ለማየት እንደናፈቀ አለ። ዛሬም የተጫነበትን የጠባብ ቡድን ኢዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ከጫንቃው ላይ አሽቀንጥሮ ለመጣል ትግሉን እያጧጧፈ ያለው የናፈቀውን ራዕይ ዕውን ለማረግ መሆኑ ሊሰመርበት ይገባል።

ኢሕአፓም ይህን የሕዝብ ራዕይ ዕውን ለማረግ በሚደረገው ትግል እንደእስካሁኑ ከሕዝብ ጎን ቆሞ የሚጠይቀውን መስዋዕትነት ለመክፈል፤ በታኅሳስ ከዚያም በኋላ በተሰውትና ዛሬም ባደባባይ እየረገፉ ባሉ ወጣቶች፤ ባጠቃላይ ለዚያ ራዕይ በተሰው ዜጎች ስም ቃል ኪዳኑን ያድሳል።

**ኢትዮጵያ በወጣት ልጆቿ ተጋድሎ ዴሞክራሲን ትጎናጸፋለች!!**
**ሀገራችን በነፃነት ለዘላለም ትኑር!!**